# የህግ ትምህርት ማሻሻያ ፕሮግራም አተገባበር

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ኢሳያስ አየለ

1. የመምህራን ተነሳሽነት ከፍ ለማድረግ በመምህራኑ በኩል የተዘረዘሩት ለምሳሌ የስራ ጫና፣ለምርምር የሚመደብ ገንዘብ አጠቃቀም ዙሪያ የሚስተዋሉ የአስተዳደር ውስንነቶችን እና ሌሎችን ችግሮችን በመቅረፍ ፣ የመምህራን ተነሳሽነት ከፍ ማድረግ ፣ ለህትመት የሚያግዙ ተቋማዊ ሁኔታዎችን ለምሳሌ ያህል የማተሚያ ቤቶችን የማጠናከር ሥራዎች መሰራት አለባቸው ፡፡

2. ለምርምር እየሰጡት ያለውን ትኩረት በማጠናከር ያሉባቸውን ድክመቶች በማስወገድ ለምርምር ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር ይኖርባቸዋል ፡፡

3. በፋይናንስ አስተዳደር በኩል ያለውን ውጣ ውረድ በመቀነስ እንዲሁም የመምህራን የስራጫና በመቀነስ ለምርምር የሚሰጡት ሰአት ከፍ እንዲያደርጉ ማመቻቸት ይኖርባቸዋል ዋል ፡፡

4. ዝቅተኛ አፈጻጸም የሚታይባቸውን የተማሪችን ተሳትፎ፣ የመምህራን የማስተማር ተነሳሽነት ከፍ የሚልበት ሁኔታ ሊመቻች እና በዚህ ላይ የተጠናከረ ስራ ሊሰራ ይገባል፡፡ አዳዲስ ተማሪዎች በሚገቡበት ወቅት ስለ ዩንቨርስቲ የትምህርት ዓለም የሚረዱበት የምክር አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ መጠናከር አለበት ፡፡

5. የትምህርት ማጣቀሻ መጻህፍት ላይ ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሰራበት ይገባል ፡፡

6. የማህበረሰባዊ አገልግሎት እየሰጡ የሚገኙት በተጠናከረ ሁኔታ የሚሰጡት ሁኔታ ማስቀጠል ሲኖርባቸው ዝቅተኛ አፈጻጸም ያላቸው የትምህርት ክፍሎች እራሳቸውን በመፈተሽ ጠንካራ ልምድ ካላቸው ልምድ በመቅሰም ራሳቸውን ማጠናከር ይኖርባቸዋል ፡፡

7. በስርዓተ ትምህርት ላይ ያሉትን ጠንካራ ጎን ማስቀጠል ፣ እንዲሁም በስርዓተ ት/ት ትግትግበራ ማሻሻያ ላይ ባለድርሻ አካላትን የማሳተፉ ልምድ ማደግ ያለበት፡፡በመሆኑም የትምህርት ክፍሎቹ ያለው ጠንካራ ጎን በማጎልበት የሚስተዋሉ ውስንነቶች የሚስተካከሉበት ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡